# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የጉምሩክ ኮሚሽን
# THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
# CUSTOMS COMMISSION


ቀን ነሐ 2 6 2012
Date
ቁጥር 4-0/0170/
Ref.No.

በአባሪው ለተዘረዘሩት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡ <u>መመሪያ ቁጥር 153/2011 በመመሪያ ቁጥር 170/2012 የተሻሻለ መሆኑን ስለማሳወቅ፤</u>

የገቢዎች ሚኒስቴር በቁጥር 1/14/12 ነሃሴ 23 ቀን 2012 በተጻፈ ደብዳቤ የጉምሩክ አስተላላፊነት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ እና በአስተላላፊዎች ጥፋት ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 153/2011 በመመሪያ ቁጥር 170/2012 የተሻሻለ መሆኑን አሳውቋል፡፡

በመሆኑም የጉምሩክ አስተላላፊነት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ እና በአስተላላፊዎች ጥፋት ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 153/2011 በመመሪያ ቁጥር 170/2012 የተሻሻለ መሆኑ ታውቆ በዚሁ አግባብ እንዲፈጸም እያሳሰብን፤ የመመሪያውን ኮፒ 09 ገጽ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

መ/ሊ አብዲሳ ኢ/ቾ
የጉምሩክ ኮሚሽን ጽ/ቤት ኃላፊ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Customs Commission No.2

ግልባጭ፤
- ለኦፐሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
  <u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>



☎ +251 116 62 98 00
+251 116 62 98 19
✉ 2559
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia

- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞጆ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመቀሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሐዋሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅግጅጋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዋሽ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞያሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጋላፊ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአሶሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሠመራ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅቡቲ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
- ለታጁራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

<u>በያሉበት</u>፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገቢዎች ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF REVENUES

ቀን 1 ሐሴ 23 2012
Date
ቁጥር 1/14/12
Ref.No

ለጉምሩክ ኮሚሽን

አዲስ አበባ

ጉዳዩ:- የመመሪያ ማሻሻያ ስለመላክ፤

የጉምሩክ አስተላላፊነት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ እና በአስተላላፊዎች ጥፋት ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 153/2011 በመመሪያ ቁጥር 170/2012 የተሻሻለ ስለሆነ በማሻሻያው መሠረት እንዲፈፀም አሳስባለሁ።

ከሠላምታ ጋር

ላቀ አያሌው አንተነህ
ሚኒስትር

Phone: +251 11 662 98 00/ 01/02/03/04/05/06/07/08 Fax: +251 11 662 98 17
face book page: ministry of revenues. FBP: mor Ethiopia Twitter: erca@twitt
web site: http//www:erca.gov.et P.o. Box: 2559 Addis Ababa, Ethiopia

የበለፀገች ኢትዮጵያ!

## የጉምሩክ አስተላላፊነት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ እና በአስተላላፊዎች ጥፋት ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 153/2011 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 170/2012

የመመሪያ ቁጥር 153/2011ን ከደንብ ቁጥር 108/1996 ጋር ለማጣጣም በማስፈለጉ ይህን የማሻሻያ ማውጣት አስፈልጓል፡፡

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የጉምሩክ አስተላላፊነት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ እና በአስተላላፊዎች ጥፋት ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 153/2011 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር170/2012" ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡

2. ማሻሻያ

መመሪያ ቁጥር 153/2011 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1/ የመመሪያው አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ (1) ተሰርዞ በሚከተሉት ንዑስ አንቀጾ (1) እና (2) ተተክቷል፡፡

(1) በግለሰብ ለሚሰጥ የጉምሩክ አስተላለፊነት ሥራ ፈቃድ ለማውጣት ከባለመብቱ በተጨማሪ

ቢያንስ አንድ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያለው ሰው መቅጠር ይጠበቅበታል፤

(2)በድርጅት ለሚሰጥ የጉምሩክ አስተላለፊነት ሥራ ፈቃድ ለማውጣት የጉምሩክ አስተላላፊነት

የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያላቸው ቢያንስ ሁለት ሰዎች መቅጠር ይጠበቅበታል፤

2/ የመመሪያው አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ (2) ፣ (3) እና (4) እንደ ቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጾ (3) ፣ (4) እና (5) ሆነዋል፡፡

3/ የመመሪያው አንቀፅ 20 ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) ተሰርዘው በሚከተለው አዲስ አንቀፅ ተተክቷል፡፡

(1) በጉምሩክ አስተላላፊነት ስራ ላይ ለመሰማራት የጉምሩክ አስተላላፊነት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም የጉምሩክ አስተላላፊ እንደአስፈላጊነቱ ኮሚሽኑ የሚወስነውን ዋስትና የማቅረብ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

4/ የመመሪያው አንቀፅ 20 ንዑስ አንቀፅ (3) የመመሪያው ንዑስ አንቀፅ (2) ሆናDል፡፡

3. ማሻሻያ መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በኢፌድሪ ገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ሰኔ ... ቀን 2012 ዓ.ም

ላቀ አያሌው

የኢፌድሪ ገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር

Customs Commission

Records Documentation

# መግለጫ

የጉምሩክ አስተላላፊነት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ እና በአስተላላፊዎች ጥፋት ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 153/2011 ፀድቆ ስራ ላይ መዋሉ ይታወቃል፡፡

ሆኖም ግን በመመሪያው አንቀፅ 9 ንዑስ እንቀፅ (1) በጉምሩክ አስተላላፊነት የስራ ዘርፍ ለመሰማራት የሚያስፈልገውን ሙያ ብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ዋና ዋና መስፈርቶች ውስጥ የሙያ ማረጋገጫ ሠርተፊኬት ያለው 4 ሰው መቅጠር እንደሚስፈልግ ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን የጉምሩክ አስተላላፊዎች የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 108/1996 አንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ (ሐ) ላይ 2 ሰው በሚል የተደነገገ በመሆኑ ከመስፈርቱ ጋር የሚጋጭና ማሻሻያ የሚስፈልገው ነው፡፡ በሌላ በኩል በመመሪያው አንቀፅ 20 ንዑስ አንቀፅ (1) ዋስትናን በተመለከተ ከአዲስ አበባ ከተማ፣ ከድሬዳዋ ከተማ፣ ከአምራቾች፣ ከግዙፍ የንግድ ኩባኒያዎች፣ ከትራንዚተሮች ከዕቃ አስተላላፊዎች ማህበራት የጉምሩክ አስተላላፊነት ፈቃድ የተሰጣቸው ማንኛውም የጉምሩክ አስተላላፊዎች በጉምሩክ አስተላላፊነት ስራ ለመሰማራት በጥሬ ገንዘብ ወይም በባንክ ጋራኒቲ ወይም በኢንሹራንስ ቦንድ 100,000 (አንድ መቶ ሺ.ህ ብር) ዋስትና ማቅረብ እንዳለባቸው እንዲሁም በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) ከብሔራዊ መንግስታት ወይም የጉምሩክ ሰራተኞች የነበሩ ሆነው ስምንት ዓመትና ከዚያ በላይ ያገለገሉ የጉምሩክ አስተላላፊነት ፈቃድ የተሰጣቸው ሰዎች በጥሬ ገንዘብ ወይም በባንክ ጋራኒቲ ወይም በኢንሹራንስ ቦንድ 50,000 (ሃምሳ ሺ.ህ ብር) ዋስትና ማቅረብ እንዳለባቸው የተደነገገ ሲሆን ይኸው ድንጋጌ በደንብ ቁጥር 108/1996 አንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ (መ) ላይ በየጊዜው እንደአስፈላጊነቱ በባንክ ሂሳብ ውስጥ እንዲቀመጥ የሚወስነው ገንዘብ ወይም ተቀባይነት ያለው ዋስትና በሚል ተደንግጓል፡፡ይህም በአጠቃላይ በደንቡና በመመሪያ መካከል ግጭት መኖሩን የሚያሳይ በመሆኑ ለማሻሻያው ምክንያት ሆኗል፡፡

ለ፦ ክብር ሚኒስትር

ከ፦ ህግ አማካሪ

ቀን፦ ነሐሴ 21/2012 ዓ.ም

ጉዳዩ፦ ለጉምሩክ መመሪያ ቁጥር 153/2011 ማሻሻያ የቀረበ ማብራሪያ፤

የጉምሩክ አስተላላፊነት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥና በአስተላላፊዎች ጥፋት ላይ የሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ቁጥር 153/2011 ለማሻሻል በቀረበው ረቂቅ መመሪያ ላይ የሚከተለው ማብራሪያ ቀርቧል፡፡

1. የሰው ኃይል ቅጥር ቅድመ ሁኔታዎችን በተመለከተ

መመሪያ ቁጥር 153/2011 ተብሎ የሚታወቀው የጉምሩክ አስተላላፊዎች የብቃት ማረጋገጫና የዲስፕሊን መመሪያ በዋናነት አንድ ሰው የጉምሩክ አስተላላፊ ሆኖ ለመስራት በቂ የቢሮ ፋሲሊቲዎችንና የሰው ኃይል ማሟላት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ በጉምሩክ አስተላላፊዎች ደንብ ቁጥር 108/1996 ላይ ጭምር ተደንግጎ ይገኛል፡፡

በዚህ መሰረት የጉምሩክ አስተላላፊ ሆኖ የሚሰራ ማንኛውም ሰው ቢያንስ ሁለት የጉምሩክ አስተላላፊነት የሙያ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያላቸው ባለሙያዎችን መቅጠር እንዳለበት በደንብ ቁጥር 108/96 የተደነገገ ሲሆን ደንቡ በግለሰብ የጉምሩክ አስተላላፊዎችና በድርጅት የጉምሩክ አስተላላፊዎች መካከል ልዩነት አላደረገም፡፡ በዚህ መሰረት በአሁኑ ሰዓት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ የሚገኘው የጉምሩክ ረቂቅ ደንብ በግለሰብ የጉምሩክ አስተላላፊዎችና በድርጅት የጉምሩክ አስተላላፊዎች መካከል የሰው ኃይል ቅድመ ሁኔታዎችን በሚመለከት የተለያዩ መመዘኛዎችን አስቀምጧል፡፡ ይኸውም የጉምሩክ አስተላላፊ ድርጅት የጉምሩክ አስተላላፊነት የሙያ ብቃት ያላቸው አራት ባለሙያዎችን መቅጠር እንዳለበትና ግለሰብ የጉምሩክ አስተላላፊዎች ደግሞ ሁለት የጉምሩክ አስተላላፊነት የሙያ ብቃት ያለቸው ባለሙያዎችን ብቻ መቅጠር እንዳለባቸው በመጀመሪያው ረቂቅ ላይ የደነገገበት ነበር፡፡

በዚህ ጊዜ የጉምሩክ መመሪያ ቁጥር 153/2011 ጎን ለጎን እየተዘጋጀ ስለነበረና ደንቡ በአጭር ጊዜ ጸድቆ ይወጣል ከሚል መነሻ በመመሪያ ቁጥር 153/2011 ላይ በደንቡ ረቂቅ ለድርጅት

አራት፤ ለግለሰብ የጉምሩክ አስተላላፊ ደግሞ ሁለት ባለሙያ መቅጠር እንዳለባቸው የሚደነግገውን በመውሰድ እንዲካተትበት ተደረገ።

ነገር ግን በሂደት የጉምሩክ ደንብ በገቢዎች ሚኒስቴር እና በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል በጋራ እንዲቀርብ ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በተገለጸልን መሰረት የደንቡ ረቂቅ ለገንዘብ ሚኒስቴር እንዲቀርብ በመደረጉ በኋላ ገንዘብ ሚኒስቴር የጉምሩክ አስተላላፊዎችን በድጋሚ ጠርቶ እኛ ባለንበት አወያየ። በውይይቱ ወቅት የጉምሩክ አስተላላፊዎች ያነሱትና አጥብቀው የተከራከሩበት ነጥብ የደንብ ቁጥር 108/1996 ለድርጅት አስተላላፊዎችም ጭምር ሁለት ባለሙያ ብሎ ያስቀመጠውን የሰው ኃይል መመዘኛ ለምን ወደ አራት ከፍ እንዲል ተደረገ? የሚል ነበር። ጉዳዩን ከወጪ አንጻር በመመልከት አጥብቀው የተከራከሩበት በመሆኑ ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር ተወያይተን መመሪያው እንደሚሻሻል ታሳቢ በማድረግ የጉምሩክ አስተላላፊው ድርጅት ከሆነ ሁለት ባለሙያ እንዲቀጥር፤ የጉምሩክ አስተላላፊው ግለሰብ ከሆነ አንድ ባለሙያ ብቻ እንዲቀጥር በሚል ተስማምተን በረቂቅ ደንቡ ላይ ማስተካከያ በማድረግ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በድጋሚ አቀረብን።

በጉምሩክ ረቂቅ ደንብ ላይ ከላይ የተገለጸው ማስተካከያ ከመደረጉ በፊት ግን መመሪያ ቁጥር 153/2011 የጉምሩክ አስተላላፊው ድርጅት ከሆነ አራት ባለሙያ እንዲቀጥር እና የጉምሩክ አስተላላፊው ግለሰብ ከሆነ ሁለት ባለሙያዎች እንዲቀጥር የሚለውን መመዘኛ ይዞ ፀድቆ ነበር። ደንቡ ሳይጸድቅ መመሪያው አስቀድሞ መፅደቁ ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር ተስማምተን በጉምሩክ ረቂቅ ደንብ ላይ ባቀረብነው ማሻሻያ መሰረት መመሪያ ቁጥር 153/2011 ላይ ማስተካከያው ሳይደረግ መፅደቁ ስህተት ነበር።

ስለዚህ አሁን በሥራ ላይ ያለው መመሪያ ቁጥር 153/2011 መሰረት የሚያደርገው ያልፀደቀውን የጉምሩክ ደንብ ሳይሆን ቀደም ሲል ይሰራበት የነበረውን የጉምሩክ አስተላላፊዎች ደንብ ቁጥር 108/96 በመሆኑ መመሪያው ከጉምሩክ አስተላላፊዎች ደንብ ቁጥር 108/96 ጋር መጣጣም ይኖርበታል። ከዚህም በተጨማሪ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በቀረበው የጉምሩክ ደንብ ረቂቅ ላይም ከላይ በተገለጸው ሁኔታ መመሪያው ከፀደቀ በኋላ ማስተካከያዎች የተደረጉበት ስለሆነ መመሪያው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ለመፅደቅ ከሚጠባበቀው እና በሥራ ላይ ካለው ደንብ ቁጥር 108/96 አንፃር መሻሻል ያለበት መሆን ለመመሪያው የማሻሻያ ጥያቄ ምክንያት ሊሆን ችሏል።

ቁጥር 2
No.2
Customs Commission
Records Documentation

ስለሆነም አሁን በስራ ላይ ያለው የጉምሩክ አስተላላፊዎች ደንብ ቁጥር 108/96 ማንኛውም ሰው በጉምሩክ አስተላላፊነት ለመስራት የጉምሩክ አስተላላፊነት ሥልጠናና ፈተና ወስደው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሰጣቸው ሁለት ባለሙያዎች መቅጠር አለበት በማለት ከደነገገው ጋር መመሪያውን ለማጣጣም ለድርጅት የጉምሩክ አስተላላፊ አራት የሚለውን የባለሙያ ብዛት ወደ ሁለት እንዲሁም ለግልሰብ የጉምሩክ አስተላላፊ ሁለት የሚለውን የባለሙያዎች ብዛት ወደ አንድ ዝቅ በማድረግ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡

እዚህም ላይ ክቡርነትዎ በግልጽ እንዲገነዘቡት የሚፈለገው አሁን በስራ ላይ ያለው የጉምሩክ አስተላላፊዎች ደንብ ቁጥር 108/96 ለግለሰብ የጉምሩክ አስተላላፊዎችም ጭምር የሚያስቀምጠው የሰው ኃይል መመዘኛ ሁለት ባለሙያዎችን መቅጠር ነው፡፡ ይህ የሆነው የጉምሩክ አስተላላፊዎች ደንብ ቁጥር 108/96 በድርጅትና በግለሰብ የጉምሩክ አስተላላፊዎች መካከል ልዩነት ሳያደርግ ቅደመ ሁኔታውን ያስቀመጠ በመሆኑ ነው፡፡

ስለሆነም አሁን በመመሪያ ቁጥር 153/2011 ላይ እንዲደረግ ከተጠየቀው ማሻሻያ መካከል ግለሰብ የጉምሩክ አስተላላፊዎች አንድ የጉምሩክ አስተላላፊ ባለሙያ እንዲቀጥር የሚጠይቅ በመሆኑና ደንብ ቁጥር 108/96 ግለሰብ የጉምሩክ አስተላላፊ መቀጠር አለበት ብሎ ያስቀመጠው ሁለት ባለሙያ በመሆኑ የመመሪያው ማሻሻያ አንቀጽ 2(1) አሁንም ጥያቄ ሊያስነሳ የሚችል ነው፡፡ በመሆኑም ማሻሻያው እንደቀድሞው በድርጅትና በግለሰብ የጉምሩክ አስተላላፊዎች መካከክል ልዩነት ሳይደረግ ማንኛውም በጉምሩክ አስተላላፊነት ለመስራት የሚፈልግ ሰው ሁለት የጉምሩክ አስተላላፊነት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያላቸው ባለሙያዎችን መቅጠር አለበት የሚለውን ይዞ መሄድ ሊያስፈልግ ይችላል፡፡

በግለሰብ የጉምሩክ አስተላላፊ እና በድርጅት የጉምሩክ አስተላላፊ መካከል ልዩነት የሚፈጥረውና ለድርጅት ሁለት፤ ለግለሰብ የጉምሩክ አስተላላፊ ደግሞ አንድ ባለሙያ መቅጠርን የሚደነግገው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የቀረበው ረቂቅ ደንብ ነው፡፡ መመሪያው በዚህ መሰረት እንዲሻሻል የተደረገው የጉምሩክ አስተላላፊውን የሚጠቅም ስለሆነ ጥያቄ ሊያስነሳ የማይችል በመሆኑና በሚኒስትሮች ምክር ቤት የቀረበው ደንብ ሲፀድቅ መመሪያውን በድጋሚ ማሻሻል አስፈላጊ እንዳይሆን በማሰብ ነው፡፡ በድርጅትና በግለሰብ የጉምሩክ አስተላላፊዎች መካከል ልዩነት እንዲኖር የተፈለገው ከፍትሃዊነት አንፃር እና ለድርጅቶች የተፈቀደን ዝቅተኛ የታክስ ምጣኔ ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

ድርጅቶች ግለሰብ ግብር ከፋዮች ግብር ከሚከፍሉበት ከፍተኛ የታክስ ምጣኔ 35% የታክስ መክፈያ ምጣኔ 30% የተቀመጠላቸው የንግድ ሥራቸውን በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት በማስደገፍ ዘመናዊ አሰራርን ስለሚከተሉ ለታክስ አስተዳደሩ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ከሚለው በተጨማሪ ከግለሰቦች ይልቅ ድርጅቶች የተሻለ የስራ ዕድል ይፈጥራሉ ከሚል የፖሊሲ መነሻ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

ስለሆነም ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በቀረበው የጉምሩክ ደንብ ረቂቅ ላይ የድርጅት እና የግለሰብ የጉምሩክ አስተላላፊዎች በሚቀጥሩት የሰው ኃይል ላይ ልዩነት እንዲደረግ የተፈለገው የታክስ እና የማህበራዊ ፖሊሲ መነሻዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ የንግድ ሥራ በድርጅት መልክ እንዲሰራ የሚፈለግበት ሌላው ምክንያት ዕውቀትንና ካፒታልን በማቀናጀት የተሻለ መዋለንዋይ ኢንቨስት ለማድረግ የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡

ስለሆነም ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የቀረበው የጉምሩክ ደንብ ረቂቀ እነዚህን የፖሊሲ ታሳቢዎች መሰረት በማድረግ በድርጅት የጉምሩክ አስተላላፊና በግለሰብ የጉምሩክ አስተላላፊ መካከል ልዩነት በመፍጠር ድርጅቶች ሁለት ባለሙያዎችን ግለሰብ የጉምሩክ አስተላላፊዎች ደግሞ አንድ አንድ ባለሙያ መቅጠር እንዳለባቸው ደንግጓል፡፡

ስለሆነም በመመሪያ ቁጥር 153/2011 ማሻሻያ ላይ በድርጅት የጉምሩክ አስተላላፊና በግለሰብ የጉምሩክ አስተላላፊዎች መካከል ልዩነት በመፍጠር በጉምሩክ አስተላላፊዎች ደንብ ቁጥር 108/96 ላይ ከተደነገገው ለየት ባለመልኩ ግለሰብ የጉምሩክ አስተላላፊዎች አንድ አንድ ባለሙያ ብቻ እንዲቀጥሩ ማሻሻያ የተጠየቀበት ምክንያት የፖሊሲ ታሳቢዎችንና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የቀረበውን የጉምሩክ ደንብ ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

2. <u>የዋስትና ቅድመ ሁኔታን በሚመለከት</u>

በጉምሩክ መመሪያ ቁጥር 153/2011 ላይ ከቀረቡት ሁለት የማሻሻያ ጥያቄዎች መካከል ቀጥለን የምናየው የጉምሩክ አስተላላፊዎች የጉምሩክ አስተላላፊነት ፈቃድ ለማግኘት ማቅረብ ያለባቸውን ዋስትና የሚመለከት ነው፡፡

በመመሪያ ቁጥር 153/2011 አንቀጽ 20/1/ ላይ እንደተደነገገው ትልልቅ የጉምሩክ አስተላላፊዎች /በዝርዝር ተቀምጠዋል/ በጉምሩክ አስተላላፊነት ሥራ ለመስማራት በጥሬ ገንዘብ፣ በባንክ ጋራንቲ ወይም በኢንሹራንስ ቦንድ 100,000 ብር ዋስትና ማቅረብ እንዳለባቸው ሲደነግግ የጉምሩክ ሰራተኞች የነበሩና ከአምስት ዓመት በላይ ያገለገሉ መስሪያ

ቁጥር 2
No.2
Ethiopia Customs Commission
Records Documentation

ቤቱን ለቀው የጉምሩክ አስተላላፊ ሆነው ለመስራት 50,000 ብር በተመሳሳይ ዋስትና ማቅረብ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡

ሆኖም ዋስትናን በተመለከተ የጉምሩክ አስተላላፊዎች ደንብ ቁጥር 108/9 የዋስትና መጠንን ሳይገልጽ በጉምሩክ አስተላላፊነት ለመስራት የጉምሩክ አስላላፊዎች በባንክ ሂሳባቸው ውስጥ የሚቀመጥ ጥሬ ገንዘብ ወይም ተቀባይነት ያለው ሌላ ዋስትና ማቅረብ እንዳባቸወ የሚደነግግ በመሆኑ የዋስትናውን መጠን የሚወስነው በወቅቱ የነበረው የኢትዮጵያ ጉምሩክ ለባስልጣን ነው የሚል መነሻ በመውሰደ በአሁን የመመሪያው ማሻሻያ ላይ ማንኛውም የጉምሩክ አስተላላፊ እንዳስፈላጊነቱ ኮሚሽኑ የሚወስነውን ዋስትና ማቅረብ ያለበት መሆኑን ይደነግጋል፡፡

በእርግጥ በአሁኑ ወቅት የጉምሩክ መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን ያለው የገቢዎች ሚኒስቴር በመሆኑ ሚኒስቴሩ የዋስትናውን መጠን ራሱ በመመሪያ ሊወስን ወይም ደግሞ ኮሚሽኑ እንዲወስነው በመመሪያው ላይ ሥልጣኑን ሊያስተላልፈለት ይችላል፡፡ ስለሆነም የመመሪያው ማሻሻያ የጉምሩክ አስተላላፊው ማቅረብ ያለበትን የዋስትና ዓይነትና መጠን ኮሚሽኑ እንደየተጨባጭ ሁኔታው እያየ እንዲወስን ለኮሚሽኑ ሥልጣን የሚሰጥ ነው፡፡

የዋስትናው መጠን ከመመሪያ ቁጥር 153/2011 በፊት በነበረው መመሪያ ላይ አንድ መቶ ሺህ ብር ተብሎ በግለጽ ተወስኖ የነበረ ሲሆን የጉምሩክ አስተላላፊዎች በየጊዜው በሚያቀርቡት ቅሬታ ሁሉንም የጉምሩክ አስተላላፊዎች በጅምላ ፈርጆ አንድ መቶ ሺህ ብር ዋስትና መጠየቅ ተገቢ እንዳልሆነ በመግለጽ የዋስትናው መጠን እንደጉምሩክ አስተላላፊው አቅምና እነደእንቅስቃሴው ስፋት እየተገናዘበ መወሰን እንዳለበት ሲገልጹ ቆይተዋል፡፡

አሁን ኮሚሽኑ ያቀረበው የመመሪያው ማሻሻያ የጉምሩክ አስተላላፊዎች በየጊዜው የሚያቀርቡትን ቅሬታ መነሻ ያደረገ ሲሆ በድርጅት መልክ የሚነቀሳሰሱና በግለሰብ ደረጃ የሚነቀሳቀሱ የጉምሩክ አስተላላፊዎች የአቀማቸው ሁኔታ እየታየ ማቅረብ ያለባቸውን የዋስትና መጠን መወሰን እንዲቻል ለማድረግ ታስቦ የቀረበ ማሻሻያ ነው፡፡

ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የቀረበው የጉምሩክ ደንብ ረቂቅ የጉምሩክ አስተላላፊዎች ማስያዝ ያለባቸውን የዋስትና ዓይነትና መጠን የገቢዎች ሚኒስቴር በመመሪያ የሚወስነው መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ይህ ማለት ከላይ እንደገለጽነው የገቢዎች ሚኒስቴር የጉምሩክ አስተላላፊዎች ማቅረብ ያለባቸውን የዋስትና ዓይነትና መጠን በመመሪያው ላይ ወስኖ ማስቀመጥ ወይም

ቁጥር 2
No.2
Ethiopian Customs Commission

ደግሞ ኮሚሽኑ ተጨማጭ ሁኔታዎችን በማገናዘብ እንዲወስን በመመሪያው ሥልጣን ሊሰጠው ይችላል ማለት ነው። በሚሻሻለው መመሪያ ቁጥር 153/2011 ላይ ቀደም ሲል የነበሩት ሚኒስትር የመረጡት የዋስትናውን ዓይነትና መጠን በመመሪያው ላይ ወስኖ ማለፍን ነው።

ስለሆነም በሚሻሻለው መመሪያ ቁጥር 153/2011 ላይ የዋስትናው መጠን 100,000 እና 50,000 ብር ሆኖ የተወሰነ ሲሆን የዋስትናው ዓይነት የጥሬ ገንዘብ ፣የባንክ ጋራንቲ ወይም የኢንሹራንስ ቦንድ እንዲሁም በመመሪያው ተወስኗል። ይህን የመመሪያውን ክፍል ማሻሻልና የዋስትናውን ዓይነትና መጠን ኮሚሽኑ እንዲወስነው የተፈለገበት ምክንያት ኮሚሽኑ ኃላፊዎች ጋር ቀደም ሲል ከነበሩን ወይይቶች መረዳት እንደተቻለው የጉምሩክ አስተላላፊዎቹ ለሚያቀርቡት ቅሬታ ምላሽ ለመስጠት ሲሆን በአፈጻጸም ኮሚሽኑን የጋጠመው ሊላ ችግርም ሊኖር ስለሚችል የሁለቱ ተቋማት የበላይ አመራሮች ቢነጋገሩበት መልካም ነው።

ለማጠቃለል ያህል የመመሪያ ቁጥር 153/2011 በሚዘጋጅበት ጊዜና ለሚኒስትሯ ቀርቦ በሚፀድቅበት ወቅት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የቀረበው የጉምሩክ ደንብ ሳይዘገይ ፀድቆ ይወጣል የሚል ታሳቢ መያዙና መመሪያው ከፀደቀ በኋላ በጉምሩክ ረቂቅ ደንብ ላይ ማስተካከያዎች መደረጋቸውና የደንቡ ሳይፀድቅ መቆየት ለተከሰቱት ችግሮች ምክንያት ቢሆንም መመሪያው የደንቡን መፅደቅ ጠብቆ እንዲፈረም አለማድረጋችን ስህተት ስለሆነ ይቅርታ እየጠየቅን የጉምሩክ መመሪያ ቁጥር 153/2011 እንዲሻሻል ጥያቄ የቀረበባቸው ሁለት ነጥቦች ከላይ የገለጽናቸው ሲሆኑ ለማሻሻያው መነሻ የሆኑትን ምክንያቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት ክቡርነትዎ በጉዳዩ ላይ የጠራ ግንዛቤ ይዘው መወሰን እንዲችሉ ይህ ማብራሪያ ቀርቧል።

ከሠላምታ ጋር

<u>ግልባጭ</u>፤

- ለጽ/ቤት

  <u>ገቢዎች ሚኒስቴር</u>

ቁጥር 2
No.2
Ethiopia Customs Commission